# ከጭፍን ድጋፍ ገንቢ ነቀፋና ትችት ይመረጣል!

ካለፉት ሦስት ወራት ወዲህ በአገራችን የሚታዬው የለውጥ ሂደት፣በጠ/ሚኒስትሩ በዶር አብይ አህመድ አንደበት የተነገረው መልካም ተስፋና በጎ ዓላማ ያዘለው ንግግርና መግለጫ የሚደገፍና መበረታታት ያለበት ነው።ምንም እንኳን ላለፉት 27 ዓመታት የሥርዓቱ አካል ሆነው ቢቆዩም፣ ያንን ፈንቅለው በመውጣት አሁን በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ እንዲመጣ ጥቂት የኦሕዴድ፣የብአዴንና በከፊልም የደቡብ ሕዝቦች ድርጅት መሪዎች አገራችን ለመፈራረስ በቋት ላይ የነበረችበትን አደጋ ለመቀልበስ ያደረጉት ትግልና የደረሱበት ውጤት በሁሉም ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድ ሊደገፍ ይገባዋል።

ይህ ማለት ግን ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ ሆኗል ማለት አይደለም።ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች አሉ፤እነዛን ግን ጠ/ሚኒስትሩና በአመራር ቦታ ላይ ያሉ ጥቂቶቹ ብቻቸውን ያጠናቅቁታል ማለት አይደለም። የአገር ጉዳይ በአንድ መሪ ፍላጎት፣ ድካምና ጥረት ብቻውን የሚጠናቀቅ ሥራ አይደለም፤በመንግሥት ደረጃ በተቋቋሙ ተቋማትና ባለሙያዎች እንዲሁም በሕዝቡ ድጋፍና ተሳትፎ የሚጠናቀቅ ጉዳይ ነው።እስከአሁን ድረስ ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በየቦታው እየሄዱ ሕዝብን በማረጋጋት፣ከአገር አገር እየዞሩም የዲፕሎማሲ ሥራዎችንና ግንኙነቶችን በማጠናከር ሥራ ላይ ተጠምደው ከርመዋል፤ብዙ ውጤቶችንም አስመዝግበዋል።በጽህፈት ቢሯቸው የተቀመጡበት ጊዜ ቢሰላ በጣም ጥቂት ነው።

በዚህ የመንከራተት ተግባር ላይ ብቻ ከተጠመዱ የጠ/ሚንስትርነቱ የቢሮ ሥራ መጓተት ብቻ ሳይሆን አሁን የወያኔ ቡድንና ቅጥረኞች የሞት የሽረት የሽብር እርምጃ በሚወስዱበት ወቅት ለአደጋም ሊጋለጡ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜም ከጠ/ሚኒስትር ተግባር ጋር ያልተያያዙ ሥራዎችን ሲሰሩ ይታያሉ፤ለምሳሌም ያህል የባህልና የትምህርት ሚኒስቴር ሊሰራው የሚገባውን የኪነት ሰዎችን ሰብስቦ የማሰልጠን ተግባር ፣ሌሎቹንም እንዲሁ የሚመለከተው ተቋም ወይም ሚኒስትር ሊሠራው ሲችል ጊዜያቸውን በዚያ ላይ ማባከን የሚገባቸው አይመስለኝም። ሌላው ትልቁ ጉዳይ መቋቋሙ የተነገረለት ግን በሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚታይ ካቢኔ አለመኖሩ ነው። የአንድ ሰው ብቸኛ ውሳኔና ፍላጎት ወይም አመራር ጎልቶ ይታያል።

ያ ደግሞ ሊያስከትል የሚችለው ትልቁ አደጋ አመራሩ የብዙሃን ተሳትፎ ከሌለው(collective leadership)ለሚሉት ባዳ ከሆነ፣በመሪው ላይ አንድ ጉዳት ቢደርስና ከቦታው ቢርቅ ስርዓቱ ውዥንብር ውስጥ ይገባና መሪ አልባ ያደርገዋል።አገራችንም ቀውስ ውስጥ ትገባለች።በወያኔ ላይ የደረሰውም ችግር ከስርዓቱ መበስበስ ባሻገር መሪ አልባ መሆኑ ነው። መለስ ዜናዊ ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ድርጅቱን እስከሞተበት ድረስ የበላይ አድርጎት ነበር፤ከሞተ በኋላ በወያኔ ውስጥ የሚተካ ሰው ወይም አመራሩ በብዙሃን ያልተዋቀረ ስለሆነ ዝርክርኩ ወጣ።አሁን ለደረሰበትም ውድቀት ተጋለጠ።

አሁን በዶር አብይ አህመድ የሚመራው መንግሥት ከተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳይወድቅ የሥራ ክፍፍሉ በተግባር ቢገለጽ፣ የአስተዳደር ተቋማት ቢጎለብቱ፣የሚወሰደው ውሳኔና እርምጃ የጋራ ቢሆን የካቢኔ አባላት ሚኒስትሮች የተሾሙበትን ሥራ በትጋት እንዲሠሩና ከሕዝቡ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ቢያድግ ጅምሩን ያሳምረዋል።

በተቋማት የዳበረ መንግሥትና አስተዳደር ያለው አገር በሚፈጠር የመሪዎች ውዝግብ ስርዓቱ አይናድም። ምርጫ ተካሂዶ ሌላ መሪና መንግሥት እስኪሰየም ድረስ ምንም ሳይጓደልና ሰላምና ጸጥታ ሳይደፈርስ ይቀጥላል። ከላይ በተዘረዘሩት ተግባሮች አንጻር ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ እስከዛሬ ድረስ አገራችን ካዬቻቸው መሪዎች የተለዩ መሆናቸው አይካድም።በተለይም ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት አገራችንን ሰንጎ ከያዛት፣ የጥፋት ሃይሎች ከመሰረቱት ስርዓት ለማላቀቅ በውስጥ አርበኝነት ከሌሎች አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የሚያደርጉት ሙከራ ልዩ ያደርጋቸዋል።

ይህ ፍላጎትና ቀናነት ግን ከሰውነት ደረጃ አውጥቶ መልአክ አያደርጋቸውም። ከሚገባው በላይ ማምለክና በጭፍኑ መደገፍ ዶር

አብይን ወደማይፈለግ አቅጣጫ ማለትም ወደ አምባገነንነት እንዳይወስዳቸው መጠንቀቅ ያሻል።ሕዝቡም ያደረገውን ትግልና የከፈለውን መስዋእትነት ያደበዝዘዋል።

እራሳቸውን ለዚህ የሥልጣን እርከን ያበቃቸው በዋናነት የሕዝቡ ትግል ሲሆን በተጨማሪም የውጭ አገር መንግሥታትና ሃይሎች ያደረጉት ስውርና ቀጥተኛ ተሳትፎ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።ዶር አብይና ቀሪዎቹ የለውጥ አራማጆች የሕዝብ ብሶት የወለዳቸው እንጂ በተአምር ከሰማይ ዱብ ያሉ የመንፈስ ልኡካን አይደሉም። ከሁሉም በላይ የሚጠብቃቸው ሥራ ሥርዓቱን ለመለወጥ ሥርዓቱ የቆመበትን ሕገመንግሥት መሻር፣ ኢሕአዴግና ክልል የተባለ ካስማ(ምሰሶ)መስበር ነው።በኢሕአዴግ መዋቅር ውስጥ ሆኖ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት ቀርቶ ማሰብ አይቻልም። 2 በክልል መንግሥትና ሕግ ስር አንዱን ባለቤት ሌላውን ባይተዋር፣አንዱን ነባር ሌላውን መጤ፣አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች በማድረግ የተቀመረው የአስተዳደር ደንብ ካልተወገደ የሚፈለገው ለውጥ እዉን አይሆንም።ለዚያ ሕዝብን ያሳተፈ ሕገመንግሥት እንዲረቅ፣የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት በሩን መክፈት ያስፈልጋል።አሁንም የወያኔ መራሹ የጥፋት ቡድን አልሞት ባይ ትግሉን በማሸበር ቀጥሎበታል።የቅዳሜው ፍንዳታ፣በየከባቢው በሲዳማ፣በአሶሳ የሚደረገው የጭፍጨፋ ሴራ የዚያ ተቀጥያ ነው።

በሌሎቹም ቦታዎች መከሰቱ አይቀርም። በወያኔ ሽብርተኞች የሚካሄደውን ሴራ ለመስበር መንግሥትና ሕዝቡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለሽብር ፈጣሪዎቹ የማያዳግም ትምህርት መስጠት ይገባዋል።ዶር አብይና አጋሮቻቸው ለአደጋ እንዳይጋለጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። በዚህ አጋጣሚ በትናንትናው ቀን የተሰማው የነዳጅ(ጋዝ)ግኝት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ዜና ነው፤እንኳን ደስ ያለን እላለሁ።ጥናቱ ተጠናቆ ምርቱ ለጥቅም እንዲውል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምኞት ነው።

እዚህ ላይ መረዳት ያለብን ግን ይህ ግኝት ትናንትና ወይም በዶር አብይ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም።ከ 45 ዓመት በፊት በንጉስ ሃይለሥላሴ ዘመን በኦጋዴን በተደረገው ቁፈራ የወጣው ነዳጅ በጠርሙስ ተሞልቶ ለንጉሱ በእጃቸው እንደተሰጠ በጊዜው በነበረው የዜና መዋቅር፣በቴሌቪዥንና ጋዜጣ በምስል ለሕዝብ መታየቱን አስታውሳለሁ።ሆኖም ግን ለምርቱ የሚወጣውና ከምርቱ የሚገኘው ገቢ እንደማይመጣጠን በቀረበው ሃሳብ ሊሰናከል ችሏል።ሌላውም ምክንያት የአረብ አገሮች ያደረጉት ተጽእኖ ነው ይባላል።

በደርግም ጊዜ የራሽያ ነዳጅ አውጭ ኩባንያ ተሰማርቶ እራሽያኖች በምርቱ ላይ ከፍተኛው ድርሻ ይኑረን በማለታቸው በተፈጠረው አለመግባባት እንዲሁም በከባቢውም በተፈጠረው አለመረጋጋት ሊቆም ችሏል። አሁን ባለው ስርዓትም ቻይናዎች ቁፈራውን ቀጥለውበት በኦጋዴን ነጻ አውጭ ነኝ ባይ የሽብር ቡድን የጥቃት እርምጃ ከሰላሳ በላይ ሰራተኞች በመሞታቸው ቁፋሮው ለጊዜው እንዲቆም ሆኖ ነበር።በዚህ የሽብርተኞች እርምጃ እንግሊዞች በመደሰት ሽብርተኛ ብለው የመደቡትን የኦጋዴንን ነጻነት ግንባር እስከማወቅና መደገፍ ደርሰዋል።አሁን በዘመነ አብይ ከዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ማየቱ ደስ ቢያሰኝም ሥራውን በዘመነ አብይ ጊዜ የተጀመረ አያደርገውም።አይደለምም። ስለሆነም የሚናፈሰው የተሳሳተ ግንዛቤ መታረም ይኖርበታል። በዚህ ዙሪያ ምስጋና ይሰጥ ከተባለ ከወያኔ በፊት ለነበሩት መንግሥታት ሊሆን ይገባዋል።

የኦጋዴንን ከርሰምድር የደፈሩት የአጼ ሃይለሥላሴና የደርግ መንግሥታት ናቸው።አሁን ዶር አብይ የገባበትን ቤተመንግሥት የቀድሞዎቹ ነገሥታት እንደገነቡት ሁሉ! ዶር አብይ አህመድ ሊመሰገኑበትና ሊወደሱበት የሚያስችሉ ብዙ ሥራዎች ይጠብቋቸዋል፤እነዚያን በተግባር ስናይ ደግሞ ከአሁኑ በበለጠ ልንደግፋቸውና ልናደንቃቸው እንችላለን።በጭፍኑ መደገፍ ግን እሳቸውንም አገራችንንም ይጎዳል።እንደ ብልህ መሪም የሚመርጡት ገምቢ ትችትን እንጂ ጭፍን ድጋፍን አይደለም ብዬ አምናለሁ።

ለወጠኑት ዓላማ መሳካት መሳሪያና ዋስትና የሚሆነው የተቋማት መጠናከርና ሥራው ተቋማዊ(institutionalized)መሆን ነው።በኢሕአዴግ የጎሳ አጥር ውስጥ ሆኖ የተሻለና የተለዩ ለውጥ አይመጣም። በአሁኑ ሰዓት በውጭ አገር ይኖሩ የነበሩ አብዛኞዎቹ የጎሳ ድርጅቶች በአገር ውስጥ በመግባት በመሰባሰብ ላይ ናቸው። የቀሩትም ለመግባት ወስነዋል።በውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙት ህብረብሔር ድርጅቶች ግን ተዝረክርከው ይገኛሉ።

ያለውን የሃይል ሚዛን ለማስጠበቅ ብሎም አገራችን ልትከተል የሚገባትን እውነተኛ የለውጥ ጎዳና ለማብሰርና ሕዝቡንም ለማደራጀት የአንድነት ሃይሉ ጨርቄን ማቄን ሳይል መግባትና ልዩነቱን አሶግዶ ግንባር ፈጥሮ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።ያ ካልሆነ በሚፈጠረው ክፍተት የጎሳ ድርጅቶች ሊጠቀሙበትና ብቸኛ ምርጫ ሆነው ሊቀርቡና ሊገለገሉበት ይችላሉ። ያለውም ሕዝብን የሚያፋጅና የሚነጣጥል ሕገመንግሥትና የክልል አወቃቀር ይቀጥላል። አገራችን የጠገበውን የጎሰኞች ጅብ አሶግዳ የራበውን የጎሰኞች ጅብ እንዳታስተናግድ በአንድነት እንጠብቅ! የተጀመረው የለውጥ ሂደት ለፍሬ እንዲበቃ እንተባበር!! ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!

አገሬ አዲስ